**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**በትግራይ የተቀሰቀሰ ከፍተኛ ተቃውሞ አስተባባሪ ናቸው የተባሉ አራት ሰዎች ታሰሩ፣ በቦረና እና በሌሎችም አካባቢዎች ሕዝቡ እየሞተ የወያኔው ተለጣፊ ኦህዴድ 18ኛ ወያኔያዊ ውልደቱን በውስኪ ተራጭቶ አከበረ፣ ወያኔ ጦሩን ወደ ዳርፋር የሚያዘምትበት ምስጢር ተጋለጠ፣ ለዘመናት ተጠብቆ የቆየው የዝቋላ አቦ እና የአሰቦት ገዳም ደን በእሳት ወደመ፣ በዘረፋ ላይ የተሰማሩ ከሃምሳ በላይ የወያኔ ፖሊሶች ዘብጥያ ወረዱ፣ በርካቶች እየከዱ ወደቤታቸው ተገዘዋል፣ በአዲስ አበባ 63 እስር ቤቶች ተገነቡ** »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ** ........................

በአዲ ወንበርታ ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ተቀስቅሶ የአካባቢው ህዝብ ተወካዮች ናቸው የተባሉ አራት ሰዎች ለእስር መዳረጋቸውን ከትግራይ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከደደቢት በረሀ ጀምሮ በትግል ላይ የነበሩ ግለሰቦች ጭምር ያሉበት ይኸው ተቃውሞ አሁን የሚኖሩበት ቦታ ለወረዳው ዋና ከተማ ቅርብ ባለመሆኑ ሌላ ቅርብ አጉራባች የወረዳ ከተማ ስላለ ወደዚያ አስተደደሩ ይቀየርልን ብለው እስከ ወያኔ መሪ መለስ ድረስ ጥያቄ ቢያቀርቡም ምንም ምላሽ ያላገኙ ሲሆን፣ ከሕዝቡ ተወክለው የተላኩት አራት ግለሰቦች ታስረው እየተንገላቱ በመሆኑ የአካባቢው ሕዝብ ቁጣውን እየገለፀ እንደሚገኝ ዘገባው ገልጿል::

በትግራይ ውስጥ በአዲ ወንበርታ ወረዳ ውስጥ የኮሊሻና ወይራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚኖሩት እነዚሁ ነዋሪዎች ለ16 ዓመታት ያህል በአዲ ወንበርታ ስምንት ሰዓታት የሚያስኬድ መንገድ እየተጓዙ ይኖሩ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ክልዕተ አውልአሎ የሁለት ሰዓት ጉዞ ብቻ በመጓዝ በቀላሉ ጉዳያቸውን ለመፈፀም የሚያመቻቸው በመሆኑ ወደዚያ ይዛወርልን ብለው ቢጠይቁም የትግራይ ርዕሰ መስተዳድር ፀጋዬ በርሄን ጨምሮ በርካታ የወያኔ ባለሥልጣናት አይቀየርም የሚል ምላሽ የሰጧቸው ቢሆንም የአካባቢው ነዋሪዎች ተስፋ ባለመቁረጥ ተወካዮቻቸውን ወደ አዲስ አበባ በመላክ ቅሬታቸውን ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ፣ ለተወካዮች ምክር ቤት ተብዬው እና በወያኔ ለተቋቋመው እንባ ጠባቂ ኮሚሽን ለተባሉት ተቋም ጥያቄ ቢያቀርቡም ምንም አይነት ምላሽ ያላገኙ ከመሆናቸው ባሻገር በአካባቢው ሕዝብ ተወክለው የመጡት አራት ሰዎች የክልሉ

ባለሥልጣናት እንዲታሰሩ በማድረጋቸው በወረዳው ከፍተኛ ተቃውሞ መቀስቀሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

ወያኔ በማሰርና በመግደል እንጂ በመነጋገር የማያምን ሰንካላ ቡድን ሲሆን ለ17 ዓመታት በበረሀ ከነመለስ ጋር በመሆን ሲታገሉ የነበሩት እነዚሁ ጥያቄ አቅራቢ የአዲ ወንበርታ ነዋሪዎች የወከልናቸው ሰዎች ካልተፈቱ ምርጫ በወረዳው እንደማይካሄድ ከማስጠንቀቃቸውም በላይ «በረሀ መስዋዕትነት ከፍለን የመጣነው የሕዝብን መብት እና ጥቅም ለማስጠበቅ እንጂ ጥቂት ግለሰቦች እነመለስን ጨምሮ እንደልባቸው እንዲፈነጩ አይደለም ፡፡ ስለዚህ በረሀውንም፣ ጫካውንም ትግሉንም እናውቀዋለን» በማለት የወያኔ ካድሬዎች ላይ ከፍተኛ ዛቻ እየሰነዘሩ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

ወያኔ ከበረሀ አብረውት ሲታገሉ የመጡትን በዲሞሽን ሰበብ ከስራ አባርሮ አምስት ሺህ ብር ከሰጣቸው በኋላ ዞር ብሎ ያለመመልከቱ ሳያንሰው አሁን ደግሞ የጠየቁትን ህጋዊ ጥያቄና የመብት ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ተወካዮቻቸውን ማሰሩ ሌላ ፈተና ውስጥ ሊገባ መፈለጉን በብስጭትና በንዴት መብታችንን በትግላችን እናስከብራለን እንዲሉ ያደረጋቸው መሆኑ ከትግራይ የደሰን ዘገባ ገልፆ ምርጫውንም በፍላጐታችን አልተመዘገብንም ምርጫም አናካሂድም በማለት ምሬት አዘል ንግግር እያስደመጡ መሆኑን ዘገባው አብራርቷል፡፡

ለስርዓቱ እድሜ ማራዘሚያ ይሆኑኛል በሚል ከየክፍለ ሀገሩ መልምሎ ያመጣቸው አዲሶቹ ፖሊሶች በዘረፋ ስራ ላይ ተሰማርተው እንዳሉ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ፡፡

በቅርቡ ሚሊኒየም በዓል ተከበረ በተባለበት ማግስት ከክፍለ ሀገር መልምሎ በሁርሶ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካስመረቃቸው 6ሺህ ያህል አዲስ ፖሊሶች መካከል አብዛኞቹ በዘረፋ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ምንጮቹ ገልፀው በርካቶች ታስረው እንደሚገኙም ይኸው ዘገባ አጋልጧል፡፡

«የሚከፈለን ደመወዝ በጣም አነስተኛ ነው፣ ቀን በሀሩር ሌሊት በቁር እየተጠበስን የረባ ቁርስ እንኳዋን ሳንበላ ይህንን የመሰለ ከባድ ሥራ ላይ መመደባችን አግባብ አይደለም ሀብታም እየበላ እኛ አንሞትም» በማለት በመሣሪያ በማስገደድ በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን እየዘረፉ አልፎ ተርፎም እየደበደቡና ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ተስፋዬ መረሣ መረጃ ቢደርሰውም አንዳችም እርምጃ ሳይወስድ ቀርቶ በቅርቡ በእንዲሁ አይነት መልክ ፖሊሶች ተደራጅተው የአንድ ባለሥልጣን ዘመድ ቤት በመዝረፋቸው ብቻ በርካቶች ታፍሰው መታሰራቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ወያኔ እንዳሻኝ አዛቸዋለሁ፣ ግደሉ ሲባሉም የታዘዙትን ይፈፅማሉ፣ የመብት ጥያቄ አያነሱም በሚል ከክፍለ ሀገር መልምሎ ያመጣቸው ፖሊሶች ከወያኔ ቀድመው የእራስ ምታት ስለሆኑበት አሰልጥኖ እንደገና እንዳይበትን ችግርና ጭንቅ ውስጥ የገባ መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል።

በአሁን ሰዓት በዘረፋ ላይ ተሰማርተው ተይዘዋል የተባሉት ከ50 በላይ ፖሊሶች በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እስር ቤት ታጉረው የሚገኙ ሲሆን በየቀኑ ቁጥራቸው እየጨመረ እንደሚገኝ ምንጮቹ ገልፀው የወያኔ ባለሥልጣናት እነ ተስፋዬ መረሣ ጉዳዩን ለመደበቅ ቢፈልጉም ምንጮቹ ግን አጋልጠዋል።

ወያኔ በአዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ዜጐች በሰበብ አስባብ እየፈጠረ በየፖሊስ ጣቢያው እያጐረ እስር ቤቶቹ ተጨናንቀው በመገኘታቸው ሌሎች 63 የፖሊስ ጣቢያዎችን ለመገንባት እቅድ ይዞ 43ቱን ያጠናቀቀ መሆኑ ታወቀ።

በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ በርካታ ዜጐች ያለአንዳች ጥፋት እየታፈሱ በአዲስ አበባ ባሉ ቁጥራቸው በበዛው እስር ቤቶች እየታጐሩ ሲሆን የእስረኞቹ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ የተነሳ እስር ቤቶችን ለመገንባት እንደቻለ የአዲስ አበባ ፖሊስ ምንጮች ገልፀው በተለይም በአሁን ሰዓት አንዴ ከወርቅ ማጭበርበር ጋር ሌላ ጊዜ ከእህል መወደድ ጋር እና ከምርጫው ጋር እያሳበቡ የአይናቸው ቀለም አላማረንም የሚሏቸውን ዜጐች እያጐሯቸው በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ በላይ የእስረኞች ቁጥር እየበዛ መምጣቱን ገልፀዋል።

በዚህም ምክንያት የአዲስ አበባ ህዝብ የእለት ጉርስ የሚበላው አጥቶ እየተቸገረ ባለበት ሰዓት ለሕዝብ ደንታ የሌለው ወያኔ የተራበውን ሕዝብ መልሶ ለማሰር ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ 43 እስር ቤቶችን የገነባ ሲሆን ቀሪዎቹ 20 ደግሞ በቅርቡ እንደሚገነቡ የፖሊስ ውስጥ አዋቂዎች አጋልጠዋል።

በተያያዘ ዜና የወያኔ መከላከያ ሠራዊት ቤተሰቦች ብቻ እህልና ዘይት የመሳሰሉ የምግብ ፍጆታዎች በቅናሽ ዋጋ እንዲገዙ መቅረቡ ከፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደገጠማቸው ለማወቅ ተችሏል።

በድብቅ ከበረሀ ለመጡ ታጋይ የጦሩ አባላት ብቻ እየተጠራሩ ጤፍ፣ ዘይትና ሳሙና በቅናሽ ዋጋ እንዲገዙ ተደርጐ ባለበት ወቅት የፌዴራል ፖሊስ አባላትና የጦሩ አባላት ጭምር በመበሳጨታቸው የተነሳ ከፍተኛ ግጭት ተከስቶ እንደነበር ዘገባው አሰረድቷል።

መስዋዕትነት በመክፈሉ ጊዜ እኛን ከፊት እያስቀደማችሁ ለማዕረግና ለጥቅማጥቅም ደግሞ እኛን እያገለላችሁ ይህን የመሰለ ስግብግብነት መፈፀሙ በጣም የሚያሳዝንና በአንድ ሀገር በአንድ ሰራዊት ውስጥ ሁለት አይነት ሕግ መኖሩን ያሳየን

በመሆኑ ትግላችን ከዚሁ ይጀምራል በማለት መሣሪያ የተማዘዙ ሲሆን አንድ የጄኔራል ማዕረግ የለበሰ ሙስሊም የአማራ ተወላጅ «ይህንን ችግር በአጭር ቀን እንቀርፋለን ስለዚህ በመቻቻል ችግሩን እንፍታው ወደ ጦሩም አይሰማ» በማለት በልመና ነገሩ እንዲበርድ ያደረገ ከመሆኑም በላይ በጦሩ አባላት መካከል ስምምነት በመጥፋቱ እደላው ከሀሙስ መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እንዳቋረጠ የደረሰን ዘገባ አብራርቷል፡፡

ይህ በሠራዊቱ ቤተሰቦች መካከል አድሏዊነት ተፈፀመ ተብሎ የተከሰተው አምቧጓሮ ጦሩ ቢሰማ ከፍተኛ ችግር ይከሰታል በማለት በቅርብ የሚገኙ የሠራዊቱን አባላት ችግሩን እንደሚቀርፉት ይህንን ስህተት የሰሩት የበታች ሹሞች በመሆናቸው እርምጃ እንደሚወሰድባቸው በመሸንገል ነገሩን ያበረዱ ቢሆንም በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉት የሠራዊቱ አባላት መካከል ከፍተኛ መከፋፈል እየተፈፀመ መሆኑንም ዘገባው ገልጿል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለ16 ዓመታት ሕዝብንና የራሴ ናቸው የሚሉትን የሠራዊት አባላት እየዋሸ የኖረ ቢሆንም ዘንድሮ ግን ውሸቱ ተጋልጦና ፀሐይ ወጥቶበት ግራ የተጋባ በመሆኑ በሁሉም የሕብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ ያተረፈና ለሠራዊቱም ተመሳሳይ ስሜት ውስጥ መግባቱን ዘገባው ያስረዳል፡፡

የወያኔው ተለጣፊ ድርጅት የኦህዴድ 18ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን በናዝሬት ባከበረ ዕለት አባዱላ በኦሮሚኛ በመናገሩ የሕወሓት ደህንነቶችና ባለሥልጣናት መበሳጨታቸው ተገለፀ፡፡

ማክሰኞ መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም በናዝሬት በተከበረው በዓል ላይ አባዱላ ገመዳ የኦህዴድ ሊቀመንበር እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት በኦሮሚኛ ንግግር በማድረጉ የተበሳጨው አዲሱ ለገሠ እና ከፍተኛ የሕወሓት ባለሥልጣናት ማስታወሻ ፅፈው ለአባዱላ ገመዳ እንዲደርሰው በማድረጋቸው አባዱላም የተሰጠውን ማስታወሻ ወረቀት እያየ «ሁሉንም ለመተርጎም እቸገራለሁ ስለዚህ አለፍ አለፍ እያልኩ በአማርኛ ለመግለፅ እሞክራለሁ» በማለት ከእነ አዲሱ የተሰጠው ትዕዛዝ መሆኑን ለተሰብሳቢው ሕዝብ ይፋ ያደረገ መሆኑም ታውቋል፡፡

የህወሓት ባለሥልጣናት በተለይ በአሁን ጊዜ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጭንቅ ውስጥ የገቡበት ወቅት በመሆኑ የራሳቸውን ጥላ ጭምር እየተጠራጠሩ በድንጋጤ እየባነኑ የሚገኙበት መሆኑን የገለፁት የደህንነት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ከ20 ዓመት በላይ ሲነዱት የነበረው አባዱላ ገመዳን እንኳዋን ሳያምኑ ቀርተው ያደረከውን ንግግር በአማርኛ ተርጉም ብለው ማዘዛቸው እጅግ አስገራሚ ከመሆኑም በላይ የፍርሀታቸው መጠንን ያሳያል ሲሉም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

በዕለቱ አባዱላ ተገድዶ እንዲተረጉም መታዘዙን ለህዝቡ ቀጥታ በሆነ አማርኛ «አሁን በኦሮሚኛ ያደረጉትን ንግግር በአማርኛ እንድተረጉመው ስለተነገረኝ ሙሉ በሙሉ በራሱ ሀሳብ አልችልም ፍሬ ሀሳቡን ብቻ አስቀምጣለሁ» በማለት በራሱ ሀሳብ ያስቀመጠ ሲሆን፣ በአንፃሩ ደህንነቶች በአባዱላ እንደተበሳጩ ምንጮቹ ገልፀው የነበራቸው ድንጋጤም ከፍተኛ እንደነበረ ገልፀዋል፡፡

እነ መለስ ሕወሓት የተመሰረተበት ነው የተባለበት ደደቢት በረሀ ድረስ ተጉዘው በትግርኛ በዓሉን ሲያከብሩ አንድም የአማርኛ ትርጉም ሳያቀርቡና እንደልባቸው ህዝባቸውን ሲቀሰቅሱ የነበረ መሆኑን የገለፁት እነዚሁ የደህንነት መ/ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ኦህዴድ በራሱ ቋንቋ በናዝሬት በማክበሩ ብቻ ፍርሀት የገባቸው ህወሓቶች ተተርጉሞ ይነበብ ማለታቸው ያሉበትን የድንጋጤ መጠን ያሳያል ሲሉ ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ገበሬው የሚበላው አለው አልተቸገረም እያለ የውሸት ድራቶውንና እንቶ ፈንቶውን ሲያስደምጥ የነበረ ሲሆን፣ ዛሬ እውነታው ወጥቶ በመጋለጡ መደበቂያና መሸሸጊያ አጥቶ የራሴ ናቸው የሚላቸው ተለጣፊ ድርጅቶችን ሳይቀር በመጠራጠር ይህን የመሰለ እና አሳፋሪ ተግባር መፈጠሩ የስርዓቱን መውደቂያ ጊዜ መቃረቡን ያሳየ ነው በማለት የናዝሬት ከተማ ነዋሪዎች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

የኦህዴድ 18ኛ ዓመት በዓል በናዝሬት ከተማ የሀውልት ምርቃት በሚል በማሊዮን የሚቆጠር ብር መቀለጃ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ በሀገሪቷ ታሪክ የመጀመሪያ ነው የተባለለትን ትልቅ ኬክ አስጋግረው ሲቆርሱ መታየታቸው የህዝብን አንጀት ያሳረረ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተገኙበት ይኸው በዓል ኬክ በመቁረስ የተጀመረ ሲሆን፣ ውስኪና ሌሎች ውድ የሆኑ መጠጦችም የዚሁ በዓል ማድመቂያ እንደነበሩ ዘገባው ገልፆ ለሆዳቸው ያደሩ ሰው መሳይ ወያኔዎች እንዲህ ባለ ሁኔታ በሀገርና በህዝብ ሀብት እየቀለዱ በዚችው ቅፅበት በሀገሪቷ ጠኔ እየጣላቸው በዚያው የሚያንቀላፉ ዜጐች በርካታ ሆነው ሳለ ይህን የመሰለ የአረመኔነት ተግባር መፈፀማቸው የሚያበሳጭ ነው ሲልም ዘገባው አክሎ ገልጿል፡፡

በቦረና ከብቶች እያለቁ የሰው ልጆች እንደ ቅጠል እየረገፉ ባለበት በዚህ ወቅት እነ አባዱላ ገመዳና አለቆቹ ኬክ እያስጋገሩ በሕዝብ ሞት ላይ እየተሳለቁ መገኘታቸው የሚያሳዝንና የሚያንገበግብ መሆኑን በቁጭት የገለፁት የናዝሬት ከተማ ነዋሪዎች ባለሥልጣናቱ ከሰኞ እለት እስከ ረቡዕ ድረስ በናዝሬት ከተማ ድሬ ሆቴል ውስጥ ሲዝናኑ እንደሰነበቱም ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ ከአይን እማኞች ገለፃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚህ በኋላ የደነበረ በቅሎ ይመስል ህወሓቶች በደረሰባቸው ፍርሀት የተነሳ የሚወስዱት እርምጃ ሁሉ የከፋ መሆኑን እና በደህንነቶችም መካከል በአሁን ሰዓት ከፍተኛ ልዩነት እየተፈጠረ መምጣቱንም ሳይሸሽጉ ገልፀዋል::

ይህንንም ሲያስረዱ የሕወሓት ደህንነቶች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ገንዘብ ሲያግበሰብሱ የነበረ መሆኑንና በተለይ ታዋቂ ነጋዴዎችን ያሰለቹ እንደነበረ ያስታወሱት ምንጮች ዛሬ ገንዘብ ሳይሆን ሕዝብ በሚፈልግበት ወቅት የሕወሓት ሰዎች ግራ ሲጋቡ በደህንነት ውስጥ ጭምር ቡድን ፈጥረው በቡድን መንቀሳቀስ መጀመራቸው ባደረባቸው ፍርሃት ጭምር መሆኑን ምንጮቹ በዝርዝር አስረድተዋል::

ከዚህ ቀደም እንደሚደረገው ጊዜ ሁሉ የሌላ ብሔር ተወላጅ የደህንነት አባሎች በግለሰብ ላይ ክትትል እንዲያደርጉ ሲታዘዙ በአሁን ሰዓት አንሠራም ለሕዝብና ለሀገር ነው የተቀጠርነው በማለት ለህወሓት ደህንነት ኃላፊዎች ምላሽ እየሰጡ በመገኘታቸው ኃላፊዎቹ ተደናግጠው እንዳሉም ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል::

ወያኔ በሁሉም አቅጣጫ ግራ እየገባው እና ለ16 ዓመታት በህዝብ ላይ በፈፀመው ግፍና በደል ምክንያት የተነሳ የሚይዘውና የሚጨብጠው አጥቶ የእውር ድንብር እየተጓዘ ሲሆን፣ አሁንም በዚሁ ባለው ጭንቀት የተነሳ በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ጦር እያዘመተና የጦር መሣሪያ እያጓጓዘ መሆኑን የመከላከያ ምንጮች ገልፀው በቅርቡም በሱዳን በኩል የአየር ላይ ቅኝት ለማድረግ እንዲያመቸው ወደ ዳርፉር ጦር ለማዝመት ዝግጅቱን ያጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል::

ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት የሚለው የወያኔ ቡድን በሱማልያ ጦሩን አስገብቶ እንዲያልቅ ያዘዙት አሜሪካኖች አሁንም ወደ ዳርፉር እንዲገባ ግንባር ቀደም ተወርዋሪ አድርገው ያዘዙት ሲሆን እነ መለስም አጋጣሚውን ተጠቅመው በድንበር አካባቢ የኢትዮጵያ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ይንቀሳቀሱበታል ተብሎ የሚጠረጠረውን ቦታ ለመቃኘትና ለመቆጣጠር እንዲችሉ ለመጠቀም ሳያደርጉ እንደማይቀር እነዚሁ የመከላከያ ምንጮች ግምታቸውን ሰንዝረዋል::

እንደ መከላከያ ምንጮቻችን ገለፃ ከሆነ በአሁን ሰዓት ከ24 ታንኮች በላይ፣ ከ5 የጦር ሒሊኮፕተሮች፣ የውሃና የነዳጅ ቦቴዎችን ጨምሮ አንቡላንስና ሌሎችንም ቁሳቁሶች በመያዝ ለጉዞ የተዘጋጀ ሲሆን ዋናው ወደ ዳርፉር ወያኔ ጦሩን ለማዝመት የፈለገው ከአለቆቹ አሜሪካኖች በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን ምንጮቹ አስረግጠው ገልፀዋል::

በዚህም መሠረት የመጀመሪያው ጉዞ የተቃዋሚ ኃይሎች በሱዳን ድንበርና በኢትዮጵያ በኩል የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው የአየር ቅኝት ለማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በእያንዳንዱ የጦር መሣሪያ የተመድ ኪራይ በየቀኑ ስለሚከፍል ከፍተኛ

ገንዘብ ለመሰብሰብ መሆኑን ምንጮች ገልፀው አንድ እግረኛ ሻለቃ ጦርም ለማዝመት እንደተዘጋጀም አጋልጠዋል፡፡

ወያኔ የሀገር ሀብትና ንብረት ማውደም የጀመረው ዛሬ ባይሆንም በአሁን ወቅት ግን ከመቼውም ጊዜ በላይ ገፍቶበት እንደሚገኝ ሁኔታውን የተከታተሉ ምሁራኖች እየገለፁ ይገኛሉ፡፡

ባለፈው ወር ውስጥ ደቡብና ኦሮሚያ ክልል ውስጥ አሉ የተባሉ ደኖች ወያኔ ለኩሷቸው ከ15 ቀን በላይ ነደው የወደሙ ሲሆን፣ በቅርቡም በዝቋላ አቦ ቤተክርስቲያንና በአሰቦት ገዳም ውስጥ ያሉት ደኖች በእሳት መውደማቸው ታውቋል፡፡

ወያኔ ገና ለገና የታጠቁ ተቃዋሚ ኃይሎች ይመሽጉበታል የሚል ፍራቻ ስላለው ብቻ አንዳንድ ጥቂት ለሆዳቸው ያደሩ ተራ ካድሬዎች ድርጊቱን እንዲፈፅሙ ትዕዛዝ በመስጠት ደኖቹን ለውድመት እያደረጋቸው ሲሆን አሁንም የዝቋላ አቦ ደን ለዘመናት በአካባቢው ህዝብና በእምነት አባቶች እንክብካቤና ጥበቃ ሲጠበቅ የነበረውን ወያኔ በቀላሉ የታጠቀ ተቃዋሚ ኃይል ያጠቃኛል በሚል ፍራቻ ደኑን እንዲቃጠል ያደረገው ከመሆኑ በተጨማሪ ደኑ አልቆ ከወደመ ከ15 ቀን በኋላ 100 የሚሆኑ ወታደሮቹን ልኮ የማስመሰያ ድራማ ሰርቶ ለማሳየት መሞከሩንም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

ወያኔ ባደረበት ፍርሀት የተነሳ የራሱ ጥላ እያስበረገገው የሚዘይዘውና የሚጨብጠው ጠፍቶት ያለ ቡድን በመሆኑ ለስልጠኔ የስጋት ምንጭ ናቸው ብሎ ያላቸውን በመሉ ከማውደምና ከማጥፋት ወደ ኋላ የማይል ቡድን መሆኑን ጠቁመው በቅርቡም በዝቋላ አቅጣጫ በኩል የአየር ኃይል ግቢውን በታጣቂ ኃይሎች ጥቃት የመሰንዘር ሙከራ ተደርጎ የነበረ መሆኑን ተከትሎ ለዘመናት ተከብሮ የኖረውን ደን እንዲቃጠል ማድረጉ የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ነው ሲሉ እነዚሁ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በ15 ቀን ውስጥ የዝቋላ አቦ ከ30 ሺህ በላይ ሄክታር ደንና የአሰቦት ገዳም ከ15 ሺህ ሄክታር በላይ ደን የወደመ መሆኑም ታውቋል፡፡

በተለይ በአሰቦት ገዳም አካባቢ ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይል ይንቀሳቀስበታል ተብሎ በወያኔ ባለሥልጣናት ዘንድ ከፍተኛ ስጋት ስላለ ጊዜንና ወቅትን ጠብቀው በከሰል አክሳዮች ስም ደን እንዲወድም ማድረጋቸውንና ገዳሙ ምድረበዳ እንዲሆን ማዘዛቸው አሳዛኝና አስደንጋጭ ነው ሲሉም የአካባቢው ነዋሪዎች እያነቡ ሲገልፁ እንደነበር ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስረድቷል፡፡

ለዘመናት ተጠብቆና ተከብሮ የኖረውን ደን ወያኔ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እያወደመ ሀገሪቱን ለምድረበዳነት የዳረጋት ሲሆን በቅርቡም ተተከለ ተብሎ የተወራለት ዛፍ የሚንከባከበው በማጣቱ ያልፀደቀ መሆኑን የገለፁት የግብርና

ባለሙያዎች በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት በዚሁ ከቀጠለ ሀገራችን ወደ በረሀነት የምትለወጥበት ደረጃ ላይ መድረሷን ያመላከተ ነው ሲሉም ስጋታቸውን ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል ኃይሌ ገ/ስላሴ በቤንጂንግ ኦሎምፒክ የማራቶን ሩጫ አልሳተፍም በማለቱ የወያኔ ባለሥልጣናት መናደዳቸውን ከሚሰጡት መግለጫዎች ለማወቅ ተችሏል።

ኃይሌ ገ/ስላሴ «ቤንጂንግ ሄጄ እራሴን አላጠፋም» በማለቱ የወያኔ ባለሥልጣናት የቻይናንና የነሱን ዲፕሎማሲ ያበላሽብናል በሚል ፍራቻ የተነሳ በኃይሌ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠሩበት እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል።

አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ባልደረባ እንዳሉት ከሆነ እነሱ ለፖለቲካ ትርፋቸው እንጂ የአትሌቱን ስጋት አልተረዱለትም ስለዚህ ነጋ ጠባ ለእኛ ትዕዛዝ እየሰጡ አሳምኑት ይሉናል እኛ ደግሞ እሱ የገባውን ስጋት እንዴት ሀሳቡን ልናስቀይረው ይቻለናል? ሲሉ ገልፀዋል።

በአሁን ሰዓት በወያኔው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን ጭምር በቀጥታና በስውር ጫና እየተደረገበት ቢሆንም ኃይሌም በአቋሙ በመፅናት በማራቶኑ ሩጫ አልሳተፍም በማለት በድጋሚ መግለጫ የሰጠ መሆኑም ታውቋል።

«የአየር ለውጡ ለኃይሌ ገ/ስላሴ ብቻ አይደለም ስለዚህ ኃይሌ የወሰደው እርምጃ የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሕግ የጣሰ ነው» በማለት ቀንደኛው ወያኔ በቻይና የወያኔ አምባሳደር ኃይሌ ኪሮስ ገሰሰ የተባለው ግለሰብም በኃይሌ ላይ የማስፈራሪያ ቃላትን እየሰነዘረበት ይገኛል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በርካታ ታዋቂ አትሌቶች ኃይሌ ይህን እርምጃ እንደሚወስድ ከገለፁ በኋላ እንደማይሳተፉ በመግለፃቸው የቻይና ባለሥልጣናት ስጋት ከቀን ወደ ቀን እየሰፋ በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ አንድ ቡድን ልከው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አማካኝነት ኃይሌን ለማሳመን ጥረት ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይገመታል ተብሎ እንደሚጠበቅም አንዳንድ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይገልፃሉ።

በአሁን ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራውን የግንባታ ሥራዎች ቻይና ከ75 በመቶ በላይ የተቆጣጠረችው ከመሆኑም ባሻገር የቀን ሠራተኛ ሳይቀር ከቻይና አስመጥታ ያሰማራች እና ለሀገር ተወላጁ ምንም አይነት የስራ እድል ያልፈጠረች መሆኗንም የአዲስ አበባ ወጣቶች በምሬት እየተናገሩ ይገኛሉ።

በመጨረሻም በአዲስ አበባ ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የማጅራት ገትር በሽታ ምልክቱ ታይቷል በአስቸኳዋይ ሕክምና (ክትባት) ይሰጣቸው በማለት የለጋሽ ድርጅቶች ሠራተኞች ለጤና ጥበቃ ሚኒስትር ባለሥልጣናትና ለእስር ቤቱ አዛዦች

ቢጠይቁም ሁሉም በየፊናቸው አይመለከተንም መድኃኒትም የለንም በማለት ሲታሹ ቆይተው በርካታ እስረኞች ለችግር ከተዳረጉ በኋላ ረቡዕ መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም ክትባት መጀመሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በርካታ የቃሊቲ እስረኞች በበሽታው ከተጠቁና ብዙዎቹ ለአልጋ ቁራኛ ከተዳረጉ በኋላ ክትባት ይሰጣቸው ተብሎ ቢጀመርም ቅድሚያ የወያኔ ፖሊስ ቤተሰቦች ክትባቱ መሰጠት አለበት በሚል ረቡዕ ዕለት የማረሚያ ቤቱን ኮሚሽነር ወዲ ሻምበልን ጨምሮ ሌሎችም ባለሥልጣናት ከነቤተሰቦቻቸው ክትባቱ እንደተሰጣቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፃ ለማወቅ ተችሏል::

በቃሊቲ እስር ቤት ከ8 ሺህ ያላነሱ እሰረኞች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉት በበሽታው ተጠቅተው በግቢው ውስጥ በሚገኘው የጤና ጣቢያ ውስጥ ሜዳ ላይ ሁሉ ሳይቀር ተኝተው እንደሚገኙ ከምንጮቹ ገለፃ ለማወቅ ተችሏል::

በተመሳሳይ በሸዋሮቢ፣ በዝዋይና በድሬዳዋ እስር ቤቶችም በሽታው ተከስቶ በርካታ እስረኞች የታመሙ ሲሆን፣ ይህ እንዳይሆን እና እንዳይከሰት አስቀድሞ መከላከል ይደረግ ብለው ሲጠይቁ የነበሩትን የለጋሽ ድርጅት ሠራተኞች ሀሳብ ወያኔዎች ሳይቀበሉ ቀርተው ዛሬ በርካታ እስረኞች ለአልጋ ቁራኛ ከተዳረጉ በኋላ ክትባቱ መጀመሩን «እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው» የሚለውን አባባል ያስታውሳል ሲሉ የእስረኛ ቤተሰቦች ይገልፃሉ::

ባለፈው ዜና ዘገባችን ላይ ይህ ችግር ሰፍቶ በርካታ እስረኞች ሊጐዳ ይችላል በሚል ሰፊ ትንታኔ ማቅረባችን አይዘነጋም::